**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የልደራ/ክ/ከተማስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት**

**ፅ/ቤት**

# የአንድ ማዕከል አገልግሎት ፤ መረጃ

# እና ትንተና ቡድን

# የ2013 በጀት ዓመት

## ዓመታዊ ዕቅድ

**መስከረም 2013 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. መግቢያ .......... 3

2. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፤ .......... **Error! Bookmark not defined.**

2.1 የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት አገራዊ ሁኔታ፤ .......... **Error! Bookmark not defined.**

2.2 የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ከተማዊ ሁኔታ እንደመነሻ፤ /የስራ ዕድል ፈጠራው ከተማዊ ሁኔታ እንደመነሻ .......... **Error! Bookmark not defined.**

2.4 የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም፤ .......... **Error! Bookmark not defined.**

2.5 የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ የአምስት ዓመት ዕቅድ (2013-2017) እንደመነሻ፤ ...**Error! Bookmark not defined.**

2.6. ጠንካራ ጎኖች እና ደካማ ጎኖች እንደመነሻ፤ .......... 17

2.7 መልካምአጋጣሚዎችናስጋቶች .......... 19

3. ራዕይ፣ተልዕኮ፤እሴት .......... 21

ራዕይ .......... 21

ተልዕኮ .......... 22

እሴቶች .......... 22

4. ስትራተጂካዊ ዓላማ .......... **Error! Bookmark not defined.**

5. ስትራተጂካዊ ግብ .......... **Error! Bookmark not defined.**

6. ዓበይት ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት፤ .......... 25

7. የአፈጻጸም አቅጣጫ፤ .......... 28

8. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና መፍትሄዎች፤ .......... 28

8.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፤ .......... 28

8.2 ችግሮችን ለመፍታት የምንጠቀመው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤ .......... 29

9. የክትትልና የድጋፍ አግባቦች .......... 29

9.1. በመስክ ወርዶ መደገፍ .......... 29

9.2 ግምገማ .......... 29

9.3 የሱፐርቪዥን ስርዓት መተግበር፤ .......... 30

9.4. የጽሑፍ ሪፖርትና ግብረ-መልስ፤ .......... 30

10 . ማጠቃለያ .......... 31

አባሪ ድርጊት መርሃ ግብር ......................................................................................................................Error! Bookmark not defined.

## 1. መግቢያ

የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት የተገልጋዮችን እርካታ በማሻሻል ለከተማው ዕድገት የድርሻውን እንዲያበረክት እና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እየሠራ ይገኛል፡፡ እንደአገር በቀጣዮቹ ዓመታት ለመፍጠር በዕቅድ የተያዘውን የሥራ ዕድልና የኢንተርፕራይዝ ልማት በማሣካት በኩል ጉልህ ድርሻ በመሆኑ ወሣኝ በሆኑ ስትራተጂያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ በመሥራት፣ ሥራዎቹን በዕቅድ በመምራት ተግባራቱን ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸምና በዘርፉ እድገት የሚጠበቀውን አስተዋጽዖ ለማበርከት የቢሮውንና በሥሩ የተደራጁ ተጠሪ ተቋማትን ግምት ውስጥ ያስገባ የቀጣይ አስር ዓመታት ከ2013 እስከ 2022 ድረስ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እንዲሁም ከ2013 እስከ 2017 ድረስ ያለውን የአምስት ዓመት ስትራተጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል ፡፡

የአንድ ማዕከል አገልግሎት፤ መረጃ እና ትንተና ዳይሬክቶሬትም ቢሮው የያዘውን ዕቅድ ለማሳካት እንዲቻል ከአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በማስተባበር ለዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ለማድረግ ይህንን ከዋናው ዕቅድ እና የዘርፍ ዕቅድ ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀውን የ2013 በጀት ዓመት የዳይሬክቶሬቱ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል ፡፡

### 1. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

### 1.1 በሀገራዊ ለውጥ ጉዞና በከተማ ደረጃ የተቀመጡ አቅጣጫዎች እንደ መነሻ

በመንግሥት ደረጃ የተካሄዱት ለውጦች የአገራችንን ህዝቦች ብቻ ሳይሆን አለምን ያስደመመ እንደሆነ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ ህዝቦች በያዙት የፖለቲካ አመለካከት፣ በዘር፣ በሐይማኖትና በሌሎችም ልዩነት ሳይደረግባቸው በአገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲፈጠር ለዚህም የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲሰፋና የተለያዩ አስተሳሰቦች መስተናገድ እንዲችሉ የሚያደርግ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ሀገርን አደጋ ውስጥ የሚከቱ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ በጥልቀት በመፈተሽና አንጥሮ በማውጣት መፍትሄ እንዲበጅላቸው የተደረገ ከመሆኑም በላይ ለዜጎቻችን ክብርን የሚያጎናጽፉና ከጎረቤት አገሮችም ጋር በሰላምና በወንድማዊ ግንኙነት ለመኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡

በዚህም ሂደት ባለፉት ሁለት አስርት አመታት በሁሉም ዘርፎች የመጡ ለውጦች ያሉ ቢሆንም የህዝቡን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እረገድ ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እንዲፈጠር እና መዋቅራዊ ሽግግሩን ሊያረጋግጥ በሚያስችል መንገድ መፈፀም ላይ በየደረጃው ያለው አስፈፃሚ እና ፈፃሚ አካላት ዘንድ ስራው የተመራበት አግባብ ጉድለት ነበረበት። በተለይም የወጣቱ የፍትሃዊ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ በተገቢው መንገድ ያልተመለሰ ስለነበር ችግሩን አባብሶት ነበር። ከዚህም በመነሳት በአገር ደረጃ እንዲሁም በከተማችን በተወሰደው የአመራር ማስተካከያ አዲስ የለውጥ አቅጣጫና እንቅስቃሴ የተፈጠረ በመሆኑ ወጣቱ የልማት ሃይል ለመሆን እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በመደመር እሳቤ የተጀመረው የብልፅግና ጉዞና የለውጥ እንቅስቃሴ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተስፋ፣ የመለወጥና የማደግ ስሜት እየፈጠረ በመሆኑ ይህንን የለውጥ እንቅስቃሴ ማስቀጠልና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል። በለውጥ አመራሩ መሪነት የሀገራችንን ዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ በሚያስችል መንገድ የተለያዩ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ተወስደዋል። በሀገር ደረጃ ተጀምረው የነበሩ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመስራት ለስራ እድል ፈጠራው ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

የከተማ አስተዳደሩ ወጣቶች በአገር ግንባታው ሂደት ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው በማመን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም ሀብት ማፍራት እንዲችሉ ሁለት ቢሊዮን ብር በመመደብ የተዘዋዋሪ ብድር እንዲጠቀሙ ተደርጓል። ከዚህ ቀደም በባለሃብቶችና በህገ-ወጥ መንገድ ሌሎች አካላት ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን በማስለቀቅ ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠሪያ እንዲሆኑ በተመሳሳይም በየአካባቢው ያለ ልማት ታጥረው የተቀመጡ ቦታዎችን በጊዜያዊነት ለስራ ፈላጊ ዜጎች ተጠቃሚነት እንዲውል አድርጓል።

ከዚህም በተጨማሪ በከተማችንም የደሀውን የህብረተሰብ የኑሮ ደረጃ ሊያሻሽሉ የሚችሉ ደሃ ተኮር ስራዎችን ህብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ እየተፈፀሙ ይገኛሉ። ለአብነትም በትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ አገልግሎት ላይ የዝቅተኛ ኑሮ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከመጥቀሙም በላይ ያለ ስራ የተቀመጡ እናቶች በምግብ ማዘጋጀት ስራ ላይ በመሰማራታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አርጓቸዋል። በሌላም መልኩ በከተማዋ የሚስተዋለውን የዳቦ እጥረት ለመፍታት የሸገር ዳቦ ፋብሪካ መገንባት የህብረተሰቡን የዳቦ የመግዛት እድል ከመፍጠሩ ጎን ለጎን በምርት ማረትና መሸጥ ስራ ላይ ወጣችና ሴቶች የስራ እድል እንዲያገኙ አድርጓል።

ወጣቶችና ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ተደራጅተው ሀብት እንዲያፈሩ ከማድረጉም በላይ የሀገር ኢኮኖሚ በማሳደግ ሂደት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው አውቀው ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ በመስራት በመዋቅራዊ ሽግግሩን የማፍጠን ሀላፊነት ሊሰጣቸው ይገባል። በዘርፍም ውጤት እንዲመጣ በአስፈፀሚውና በፈፃሚው አካል ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የአገልጋይነት ስሜት በመላበስ ለመስራት ዝግጁ የመሆን፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመጠየፍ ትግል የማድረግ፣ የሀገራዊ አንድነትን በማጎልበት በየአንዳንዱ የሥራ ክፍልና እንቅስቃሴ የመደመር መርህን ተከትሎ የመስራት፣ የተጠያቂነትና ግልጽ የሆነ የአሠራር ስርዓት በመንደፍ ስራዎችን የመስራት፣ የስራ ሰዓትን በአግባቡ በመጠቀምና አለፍ ሲልም ሰስራ ሰዓት ውጭም አገልግሎት የመስጠት፣ እርስ በርስ በመረዳዳትና በመተጋገዝ ባህልን በማጎልበት የመስራት፣ ከስራ ፈላጊው የሚነሱ ማናቸውንም አይነት ጥያቄዎች እንደየ አግባብነታቸው በጥሞና በማየት ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ አላሠራ ያሉ ማነቆዎችን በማስወገድ የአገልግሎት አሰጣጡን በላቀ ደረጃ በማሻሻል መስራት አስፈላጊ ይሆናል።

ስለሆነም የተጀመረውን ለውጥ አጠናክሮ ለማቀጠልና የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከላይ እስከታች ያለው መዋቅራችን በሙሉ አቅም በማሳተፍ የመስራት አቅጣጫን በመከተል መፈፀም ይኖርብናል።

## 1.2 የ2013 በጀት አመት የቁልፍና የአበይት ተግባራት አፈፃፀም እንደ መነሻ

### 1.2.1 የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች አፈፃፀም እንደ መነሻ

የበጀት አመቱን ስራዎችን በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም እሰፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የአመራር ዑደትን በተከተለ መንገድ ማከናወን ተችሏል። በዚህም የዝግጅት ምዕራፍ ስራችን የመጀመሪያ የነበረው በ2012 በጀት አመት በስራ እድል ፈጠራ ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን መሰረት በማድረግ በጥንካሬና በድክመት ለቀጣይ ስራ ትምህርት ሊሰጥ በሚያስችል መንገድ በየደረጃው ካሉ የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎች በተገኙበት መገምገም ነበር። በግምገማውም በአመራሩም ይሁን በፈጻሚው ዘንድ በስራ እድል ፈጠራው በተገቢው ትግልና የባለድርሻ አካላት ቅንጅት የተመራ አለመሆኑ፣ የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለውጡ በሚፈልገው ልክ የተረጋገጠ አለመሆኑ፣ ፈፃሚዎች አዲስ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ እና ውጤታማ ማድረግ የእኔ ስራ ነው በሚል እምነት ይዘው ስራዎችን አለመስራት ማደራጀትን እንደ መጨረሻ ግብ የመቁጠር፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተቀናጀ መንገድ አለመፍታት፣ የለውጥ ስራዎችን በባለቤትነት ይዞ አለመስራት፣ የተቀላጠፈ አገልግሎት አለመስጠት፣ ችግር ፈቺ የሆነ የድጋፍና

ክትትል ስርዓት አለመዘርጋት የሚሉት ጎልተው የወጡ እና የችግሮቹ ምንጭ በዝርዝር በሚለይ መልኩ ተገምግሟል።

ሌላው በዝግጅት ምዕራፍ ስራችን ያከናወነው የ2013 በጀት አመት መታቀድ ያለባቸው ልዩ ልዩ እቅዶችን የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የ2012 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸምን መነሻ በማድረግ በዘርፉ በየደረጃው በበጀት አመቱ መፈጸም የሚገባቸውን ዋና ዋና የቁልፍና አበይት ተግባራት ግቦችን የያዘ መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት ሲሆን ይህንን መሰረት በማድረግ በማዕከል የሚገኙ ሁለቱም ዳይሬክቶሬቶችና በስራቸው ያሉ ቡድኖች፣ ሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች የራሳቸውን እቅድ እንዲያዘጋጁ ተደርጓል። በተጨማሪም በዘርፉ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እራሱን የቻለ እቅድ በየዳይሬክቶሬቶቹ እንዲዘጋጅ እና የሚዘናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድም ተዘጋጅቶ እስከ ፈጻሚ ድረስ ካስኬድ ተደርጓል። የስራ እድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችል የባለድርሻ አካላት የጋራ እቅድ ተሰርቷል። ሁሉም ፈፃሚዎች ያለባቸውን ክፍተት መሰረት በማድረግ የራስን የማብቃት እቅድ አዘጋጅተዋል። በእቅድ ዝግጅት ስራችን አስፈላጊ የሆኑ እቅዶችን እንዲታቀዱ መደረጉና የእቅድ ይዘቱም ከሌሎች ጊዜ በተሻለ ደረጃ ከራስ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ እዲዘጋጅ መደረጉ እና አንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ ለመደገፍ ጥረት መደረጉ እንደ ጥንካሬ የሚወሰድ ሆኖ ማቀድ ያለባቸው አካላት በሙሉ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እቅድ አዘጋጅቶ አለማስገባት እና የሚሰጥ ግብረ መልስን ወደ ተግባር አለመቀየር ችግሮች ተስተውለዋል።

ፈፃሚን ከማብቃት አንፃር በመጀመሪያ በየደረጃው የሚገኙ የስራ እድል ፈጠራ ምክር ቤት አባላት በዕቅዱ ዙሪያ እንዲወያዩና የጋራ የተደረገ ሲሆን የአስተግባሪ ተቋማት አመራርና ፈፃሚዎች እስከታች ድረስ በየራሳቸው እንዲወያዩበት ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም በዘርፉ መሪ እቅድ ላይ በከተማ ደረጃ ለ 806 የዘርፉ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በዕቅዱ ላይ የተሻለ ግልጽነት መፍጠር ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ በተዘጋጀው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ላይ ለ759 የዘርፉ አመራርና ባለሙያዎች ግንዛቤ ማጨበጥ ስራ ተሰርቷል። በተመሳሳይም የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ፊት ለፊት ላይ አገልግሎት ለሚሰጡ አደረጃጀት ባለሙያዎች በተለያዩ መመሪያዎች፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ እና mse zone ሲስተም ስልጠና ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ በከተማ ደረጃ ባጋጠመው የበጀት እጥረት ምክኒያት ለባለሙያው መሰጠት የሚገባቸው የአቅም መገንቢያ

ስልጠናዎች ያልተሰጡ ቢሆንም የተሰጡትንም ስልጠናዎች ወደ ተጨባጭ ስራ መቀየር ላይ ውስንነቶች ተስተውለዋል።

በአጠቃላይ የዝግጅት ምዕራፍ ወቅት መሠራት የሚገባቸውን ስራዎች በመስራት ወደ ተግባር እንቅስቃሴ የገባን ቢሆንም በተቀመጠው የጊዜና የጥረት ደረጃ በመፈፀም ለተግባር ምዕራፍ አጋዥ እንዲሆን ማድረግ ላይ ውስንነት የነበረበት በመሆኑ ለቀጣይ ትምህርት ሊወሠድበት የሚገባው ጉዳይ ነው።

### 1.2.2 የዘርፉ ለውጥ ስራዎች አፈፃፀም እንደ መነሻ

በስራ ፈጠራ ዘርፍ ተደራጅተው እየሠሩ ባሉት 2 ዳሬክቶሬቶች የለውጥ ስራዎችን በከተማችን ከተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ጋር በማጣጣም ለመስራት የለውጥ ቡድንና የሞርኒንግ ብሪፊንግ አደረጃጀት በማደራጀት የየራሣቸውን የስራ ማስፈፀሚያ እቅድ አዘጋጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። አደረጃጀቶችም ቋሚ የግንኙነት ጊዜ አስቀምጠው ውይይት በማድረግ እርስ በርስ የመማማር እና ስራቸውን የመገምገም እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህም የድጋፍና ክትትል ስርዓትን በማሻሻል ወደታች ወርዶ በመደገፍ የተሠሩ ስራዎችን በአካል የማረጋገጥና ያጋጠሙ ችግሮችን ጊዜ ሣይወስዱ የመፍታት፣ በሠዓት አጠቃቀም ላይ ይስተዋል የነበረን ችግር ለመፍታት ጥረት ማድረጋቸው፣ የስራ እድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ አማራጭ የስራ እድሎችን በመለየት ወደ ስራ እንዲቀየር ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆኑ እንደ ጥሩ የሚወሰድ ሆኖ አደረጃጀቶች የተቀመጠላቸውን ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ጠብቆ ከመውያየት እና አጀንዳ አቀራረፅ ላይ ጉድለቶች ነበሩ። ይህም ደግሞ በተወሰኑ ፈፃሚዎች ዘንድ የለውጥ ስራዎችን በሙሉ ልብ ተቀብሎ ለመፈፀም ካለመፈለግ የመነጨ እንደሆነ ለማየት ተሞክሯል። ስለሆነም የተጀመረውን ለውጥ ዳር ለማድረስ በተደራጀ መልኩ ፈፃሚውን አነቃቅቶ ወደ ስራ ማስገባት አስፈላጊ በመሆኑ በቀጣዩ አመት ልዩ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል።

የ2012 በጀት ዓመት የስራ ዕድል ፈጠራ የዳሬክቶሬቱን የBSC ስኮር ካርድ በማዘጋጀት ወደ ክ/ከተማና ወደ ቡድኖች እንዲሁም ፈፃሚዎች ካስኬድ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። ከዚህ ተግባር አንፃር ስኮር ካርዱን አዘጋጅቶ ለማውረድ የተደረገው ጥረት በጥንካሬ የሚወሠድ ቢሆንም ወቅቱን ተጠብቆ የተሠራ አለመሆኑ፣ በተግባርና መለኪያ አቀራረፅ እንዲሁም ክብደት አሠጣጥ ላይ ችግሮች ተስተውለውበታል። ከስታንዳርድ ምዝገባ አንፃር በሁለቱም ዳሬክቶሬቶች የተቀመጡ ተግባራትን በስታንዳርዱ መሠረት እየመዘገቡ ለመለካት

እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ። ነገር ግን ስታንዳርዱን እየተነተኑ መለካት ላይ የሚቀሩ ስራዎች እንዳሉ በመገምገም አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሰራበት ይገኛል።

በአጠቃላይ ከለውጥ ስራዎቻችን አንፃር እየተሠሩ ያሉ ስራዎች እና የመጡ ውጤቶች ቢኖሩም ወቅቱ የሚፈልገውን የለውጥ ሂደት አመራሩ በእኔነትና በባለቤትነት መንፈስ ከመምራት አንፃር ሰፊ የሆነ ውስንነት ያለበት ነበር። ይህም ምንጩ አንድም በአመለካት ለውጥ የሚያመጣ ነው ብሎ አለመያዝ ፈፃሚው ለውጡን እንዲያሳልጥ አለመከታተል ሁለትም ስለ ሪፎርሙ የተሞላ ግልፀኝነት አለመያዝ በመሆኑ አሁን ያለውን የመደመርና የለውጥ እንቅስቃሴ ሊሸከም በሚያስችል መልኩ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅብናል።

### 1.2.3 የመልካም አስተዳደርና የብልሹ አሰራሮችን የመታገል አፈፃፀም እንደ መነሻ

በዘርፍ የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሠጣጥ ችግሮችን ለማሻሻልና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የማስፈፀሚያ እቅድ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ በማድረግ ለመፍታት ተሞክሯል። በዚህም በተለያየ ጊዜ ተደራጅተው ወደ ስራ ያልገቡ ስራ ፈላጊዎችን ችግር ከመፍታት አንፃር ወደ ስራ ያልገቡበትን ዝርዝር ምክንያት በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ለመፍታት ከፍተኛ ርብርብ ቢደረግም ችግርን ሙሉ ለሙሉ መፍታት አልተቻለም። በከተማ አስተዳደሩ የመደበውን የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ለመጠቀም ስልጠና ወስደው ህጋዊ አደረጃጀታቸውን አጠናቀው ብድሩን ለመውሰድ እየተጠባበቁ ያሉ ስራ ፈላጊዎችን ችግር ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር እየተደረገ ይገኛል። በተጨማሪም በሌሎች ምክኒያት ወደ ስራ ያልገቡትን በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተደራጁ ወደ ስራ እንድገቡ በተደረገው ጥረት እየተደረገ 181 ማህበራት 1493 ስራ ፈላጊዎች በተለያዩ ተቋማት ትስስር እንዲደረግላቸው በማድረግ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። ይሁን እንጂ ከዚህ ተግባር አንፃር የተንጠባጠቡ ጉዳቶች ያሉ በመሆኑ የቀጣይ አመት የእቅድ አካል አድረጎ መስራት ይጠበቅብናል። የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለስራ ፈላጊዎቹ ፊት ለፊት ላይ አገልግሎት ለሚሰጡ በለሙያዎች በተለያዩ መመሪያዎች፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ እና mse zone ሲስተም ስልጠና በመስጠት ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል። የአንድ ማእከል ግብአት ከፌደራል ጋር በመነጋር በተወሰነ መልኩ እንዲሟላ ተደርጓል። የስራ እድል ፈጠራና የአደረጃጀት መመሪያ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያልነበረና ሁሉም በየራሱ መንገድ የተለያዬ መስፈርት በማውጣት ለእንግልት

የሚዳርግ የነበረውን በአለፈው አመት መጨረሻ ላይ መመሪያው የተዘጋጀ በመሆኑ በዘንድሮው አመት ለፈፃሚዎች ስልጠና በመስጠት ወደ ተግባር ተገብቶ ግልፅ የሆነ የአሰራር መመሪያ እንዲተገበር ተደርጓል። ይሁን እንጂ ዘርፉ የዜጎችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሀላፊነት ያለበት እንደመሆኑ ችግሮቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ ወጣቶቹም ተጠቃሚ እየሆን አይደለም በማለት በምሬት እያነሱ መሆናቸው ገና ብዙ መስራት እንዳለብን የሚያመላክት ቢሆንም ከላይ እስከታች ያለው መዋቅራችን ለተግባሩ የሚሰጠው ግምት በተቃራኒው የመሆኑ ዝንባሌ እየሰፋ በመምጣቱ በቀጣዩ በጀት አመት በተደራጀ መንገድ በመፈፀም የወጣቶቹን ችግር መፍታት ይጠበቅብናል።

የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ኪራይ የሚታደልበት ዘርፍ በመሆኑ የሚታደለውን ኪራይ በተገቢው መምራት እንዲቻል እና በአመለካከት እና በተግባር ትግል የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በዚህ ዘርፍ የኪራይ ምንጭ ይሆናሉ የተባሉ አካባቢዎችና አሠራሮችን በመለየትና የማክሰሚያ ሰነድ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ በተግባር እንቅስቃሴ የተገኙትን በመለየት እርምጃ መውሰድ ተጀምሯል። ለአብነትም ህጋዊ ባልሆነ አደረጃጀት ሰነድ የስራ ትስስር ተደርጎላቸዋል የሚል ጥቆማ ለቢሮው ቀርቦ በጥቆማው መሰረት አስፈላጊውን ማጣራት በንግድ ቢሮና በገቢዎች ቢሮ በኩል በማድረግ ትክክለኛ ሰነድ አይደለም የተባሉትን 43 ማህበራት ትስስር እንዲታገድና እንዲቆረጥ ተደርጓል።

በየደረጃው የሚሰጡ የስራ ትስስር ስራዎች ፍትሃዊና ከብልሹ አሰራር የጸዱ እንዲሆኑ ለማድረግ ኢንተርፕራይዞቹ በተደራጁበት ቅደም ተከተል ወረፋ እንዲጠብቁና ለትስስር ሲላኩም በግልፅ ቦታ እንዲለጠፍ አፈጻጸሙን እየተገመገመ እንዲሄድ እየተደረገ ይገኛል። በተጨማሪም የሚዘጋጁና የሚላኩ ሪፖርቶች ተዓማኒና ከውሸት ሪፖርት የጸዱ መሆናቸውን በክትትልና ድጋፍ የተፈጠረውን የስራ እድል በአሰራሩን በአቅጣጫው መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ በአካል ወርዶ እየተረጋገጡ መሄድና ችግር ያለባቸውን አካላት ተጠያቂ የማድረግ ስራ ተጀምሯል። በዘርፉ የሚስተዋለውን የብልሹ አሰራርና አለአግባብ ተጠቃሚነት አመለካከትና ተግባር ትግል ተቋማዊ በሆነ መንገድ መፈፀም ላይ የሚቀር ነገር ያለ በመሆኑ በቀጣይ ሰፊ ርብርብ ማድረግ ይጠበቅብናል።

### 1.2.4 የስራ እድል ፈጠራ እና የዜጎች ተጠቃሚነት አፈፃፀም

ከተማችን አዲስ አበባ የነዋሪዎቿን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ስራ ለሌላቸው ወጣቶችና ሴቶች የስራ እድል ለመፍጠር፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየሰራች ትገኛለች። በዚህም የወጣቶችንና የሴችን የስራ እድል ተጠቃሚ ለማድረግ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በግል ባለሃብቶችና በነባር ኢንተርፕራይዞች ዘንድ ያሉ ከ437 ሺ በላይ አማራጭ የሥራ እድል መፍጠሪያ መስኮችንና አዳዲስ የንግድ ስራ ሃሳቦችን በመለየት እና ስራ እድሉ ሊፈጠርበት የሚችልበትን ዘዴ በዝርዝር በማዘጋጀት በስራ እድል ፈጠራ ምክር ቤት በማፅደቅና የሥምምነት ሰነድ በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል። ምንም እንኳን አማራጭ የስራ መስክ ልየታው አፈፃፀም የተሻለ ቢሆንም የተለዩትን አማራጮች በተዘረጋው ስልትና አሰራር በመጠቀም ለስራ ፈላጊው በአግባቡ አስተዋውቆ ስራ እንዲፈጠር ከማድረግ ይልቅ ሂዴት በመቁጠር ወደ ተግባር አለመቀየር፣ የግል ተቋማት ስራ ለመቅጠር የሚያቀርቡት የደመወዝ መጠን አነስተኛ የመሆን፣ ድርጅቶቹ የሚጠይቁትን የሰለጠነ የሰው ሃይል በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል፣ የስራ እድል እንፈጥራለን ያሉ የመንግስት ተቋማት ባቀዱት መሰረት ስራ አለመፍጠርና የስራ እድል እንዲፈጥሩ ጥብቅ ክትትል አለማድረግ ችግሮች ተስተውለዋል።

በተጨማሪም የከተማዋን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ አዳዲስ የስራ እድል የሚፈጠርባቸው የስራ መስኮችን የቢዝነስ ሃሳቦች እንዲፈልቁ በማድረግ በተመረጡ የቢዝነስ ሃሳቦችን የቪዲዮ ፕሮቶታይፕና የንግድ ስራ እቅድ በማዘጋጀት ለስራ ፈላጊው የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል።

በሌላ በኩል ባለፈው በጀት አመት በስራ ፈላጊነት ተመዝግበው ስራ ያልተፈጠረላቸውን መረጃ የመለየትና የማደራጀት እንዲሁም ከተለያዩ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው የወጡ አዳዲስ ስራ ፈላጊዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት 272,841 ስራ ፈላጊዎችን በአንድ ማእከል በመመዝገብ በተለዩ የስራ እድል አማራጮች፣ በስራ ባህል ማሳደግና ስራ ማማረጥ ዙሪያ ግንዛቤ በማስጨበጥ ለስራ ዝግጁ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። በተመሳሳይ የስራ እድል ተጠቃሚ የሚሆኑ 56,392 ወጣቶችና ሴቶችን ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት ለሚሰሩት ስራ አጋዥ በሚሆን መልኩ በተለያዩ የሙያ መስኮች በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። ይሁን እንጂ በተፈጠረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ከቁጥር አንፃር የተሻለ ቢሆንም የአመለካከት ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ደረጃ ያልተሰራ በመሆኑ በስራ ፈላጊው ዘንድ የስራ ማማረጥና መናቅ አስተሳሰቡ ያልተቀረፈ እንደሆነ ለማየት ተሞክሯል።

የከተማችንን ወጣቶችና ሴቶች የስራ እድል ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃርም በበጀት አመቱ 213,287 ቋሚ 96,819 ጊዜያዊ በድምሩ 310,106 የሚሆኑ ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከተፈጠረው የሥራ እድል

ውስጥ 246,875 (80%) ወጣቶች፣ 140,190 (45%) ሴቶች፣ 29,939 የዩንቨርስቲና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ፣ 456 የአካል ጉዳተኞች፣ 81 የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍሎች እና 152 የሥደት ተመላሽ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ከማደራጀት አንፃርም 13,680 ኢንተርፕራይዞችን በ43,062 አንቀሳቃሾች የማደራጀት ስራ ተሰርቷል። በአጠቃላይ ሲታይ የስራ እድል ፈጠራ ስራው የተሻለ አፈፃፀም የነበረው ነበር። ለዚህም የተሻለ አፈፃፀም እንደ መነሻ የሆኑት ስራው በበላይ አመራሩ ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶት የተሰራ መሆኑና በዘርፉ እስከታች ባለው መዋቅር በተቀናጀ መንገድ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አማራጭ የስራ እድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እድሎችን በመለየትና መጠቀም በመቻሉ፣ የከተማ አስተዳደሩ የወጣቶችን ወደ ስራ ለመግባት የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር በመልቀቁ የስራ እድል ፈጠራውን ማነቃቃት በመቻሉ፣ በከተማዋ በለውጥ አመራሩ መሪነት የተለያዩ ትልልቅ ፕሮጀክቶች እየተሰሩ በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የስራ እድል መፍጠራቸው፣ ከዩንቨርስቲ ተመርቀው ያለ ስራ የተቀመጡ ወጣቶችን በዜሮ አመት የስራ ልምድ በመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲቀጠሩ መደረጉ፣ የስራ እድል መፍጠር ከሚችሉ የግል ባለሃብቶች ጋር በመወያየት በቅጥር የስራ እድል እንዲፈጥሩ መደረጉ ነው።

የስራ እድል ፈጠራውን ከጥራት መለኪያዎች አንፃር ስንመለከተው የራሱ የሆነ ጉድለቶች ተስተውለውበታል። የቋሚ ጊዜዊ ምጣኔው ከእቅድ አንፃር የተሻለ ቢሆንም አጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ እድል ጋር ሲነፃፀር የ80/20 ምጣኔውን የጠበቀ ሳይሆን የጊዜዊ ምጣኔው የበዛ መሆኑ፣ ስራ ፈጠራው እድገት ተኮር ዘርፎችን ማእከል ያደረገ ሳይሆን በቅጥርና አገልግሎት ዘርፍ ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ በተመሳሳይም የሴቶች ተጠቃሚነት 50 በመቶ ማድረስ አልተቻለም። ይህ የሆነው የስራ እድል ፈጠራው አጠቃላይ ቁጥሩ ላይ እንጂ ምጣኔና ስብጥሩን ጠብቆ እየሄደ መሆኑን እየተከታተሉ ካለመሄድ የመነጨ በመሆኑ በቀጣይ ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል።

በአጠቃላይ የከተማችንን ወጣቶችና ሴቶችን የስራ እድል ፈጠራ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንፃር በየደረጃው የስራ እድል ፈጠራ ምክር ቤትና አስተግባሪ ኮሚቴ በማደራጀት አማራጭ የስራ እድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እድሎችን ከማጥናት ጀምሮ ለስራ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን የመፍታት ስራ መሰራቱ፣ ለስራ እድል ፈጠራ ስራው አጋዥ የሚሆንና የወጣቶችንና የሴቶችን የፋይናንስ ችግር ሊፈታ የሚያስችል 2 ቢሊዮን የተዘዋዋሪ ፈንድ በአስተዳደሩ መመደቡ፣ የተፈጠረውን የስራ እድል ተጨባጭነት ለማረጋገጥ በተለያየ ጊዜ የመስክ ምልከታ መሰራቱ አበረታችና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ቢሆንም ለውጡ ከሚፈልገው እና

የከተማችን ወጣት ፍላጎት አንፃር ክፍተቶችም ተስተውለዋል። በዚህም የስራ እድል ፈጠራ ስራውን ለማሳለጥ የተደራጁ አደረጃቶች ከከተማ ጀምሮ መደበኛ የግንኙነት ጊዜ በጠበቀ መልኩ ስራውን አለመገምገም፣ የስራ እድል የሚፈጥሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች በእቅዳቸው መሰረት ተግባሩን አለመፈጸምና የጠራና ተጨባጭነቱን ለማረጋጥ የሚያስችል የተሟላ መረጃ በወቅቱ አለመላክ፣ የሴቶችን ተጠቃሚነት በእቅዱ መሰረት አለመፈፀም፣ የስራ ፈላጊዎች አመለካከት ቀረጻ ስራው ቀጣይነት ያለው እና የወጣቱን ሁኔታ ያገናዘበ አለመሆኑ፣ የተለዩ አማራጭ የስራ መስኮች አሟጦ አለመጠቀም፣ አዳዲስ የስራ ዕድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ አማራጮችን አለማቅረብ፣ የትኩረት መስኮችን ማእከል አዲርጎ አለመስራት፣ ቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም በተወሰኑ ወረዳዎች ስራ ፈላጊዎቹ አደረጃጀት ስለጨረሱ ብቻ ስራ ሳይጀምሩ የስራ እድል እንደተፈጠረላቸው አድርጎ የመያዝ ዝንባሌ መኖሩ፣ በአመራሩና በፈፃሚው ዘንድ የማንንም ግፊት ሳይጠብቁ ተልእኮውን ለቅሞ ይዞ አለመፈጸም፣ በታችኛው መዋቅር ያለው ተቀናጅቶ መንቀሳቀስ በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ አለመሆን፣ ወደ ስራ የገቡትን አንቀሳቃሾች ተከታትሎ ከመደገፍና የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ከመፍታት አንጻር ያሉ ጉድለቶች በቀጣይ ተገቢው ትምህርት ተወስዶባቸው የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ መስራት ይጠበቅብናል።

### 1.2.5 የገበያ ልማት ስራዎች አፈፃፀም

ኢንተርፕራይዞች በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲወጡና ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ በገበያ ትስስር ተጠቃሚ በማድረግ በኩል በ2012 በጀት ዓመት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። በዚህም መሠረት በ2012 በጀት ዓመት በአካባቢ ገበያ 94,700 ኢንተርፕራይዞች የብር 4,890,000,000 የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ17,470(98%) ኢንተርፕራይዞች የብር 4,697,348,826 (96%) የገበያ ትስስር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በክልል ገበያ ለ150 ኢንተርፕራይዞች የብር 110,000,000.00 የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ለ214 (221%) ኢንተርፕራይዞች የብር 149,578,980 (136%) የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዉጪ የገበያ ትስስር ለ50 ኢንተርፕራይዞች የብር 56,000,000 የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ለ40( 80%) ኢንተርፕራይዞች የብር 21,475,515 (38.4%) የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በአከባቢ ገበያ ትስስር ባሳለፍነው አመት የተሻለ አፈፃፀም ቢኖርም የተፈጠረ የገበያ ትስስር ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው ጥረት ያመጡት ውጤት ሳይሆን በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የተፈጠረ መሆኑ በቀጣይ ትኩረት በመስጠት ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው በጥራት፣በዋጋና በአቅርቦት በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት መስራት ይጠበቅብናል።

የገበያ ትስስር ፍትሃዊነት ከማረጋገጥ አኳያ በገበያ ትስስር መመርያው መሰረት በቂ የገበያ ትስስር ያገኙ ኢንተርፕራይዞችን የማስወጣት ስራ የተጀመረ ቢሆም ትስስሩ እንዲቋረጥ ከማድረግ አንፃር አሁንም ብዙ ሊሰራ ይገባል። በተጨማሪምየገበያ ትስስር ሊፈጠርባቸው የሚገቡ አማራጮችን በዳሰሳ ጥናት የመለየት ስራ በዝግጅት ምዕራፍ የተሰራ ቢሆንም ተቋማት ቃል በገቡት ልክ ኢንተርፕራይዞችን ተቀብሎ ወደ ስራ ከማስገባት አንፃር ክፍተት ታይቷል።

ሞዴልጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሳተፉበትና ተሞክሮ ሊያገኙ የሚችሉባቸው 41 ጊዜ ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን በማዘጋጀት በ4,500 ኢንተርፕራይዞች 45,000,000 ብር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 33 ጊዜ ኤግዚቢሽንና ባዛር በማዘጋጀት በ2,456 ኢንተርፕራይዞች *36,633,208* ብር የገበያ ትስስር ተፈጥሯል። ባሳለፍነው በጀት አመት የኤግዚቢሽንና ባዛር አፈፃፀም በኮቪድ-19 ወረሽኝ ምክንያት በተፈለገ ደረጃ መስራት ባለመቻሉ በቀጣይ ለአምራች ኢንተርፕራይዞች ትኩረት በመስጠት ከከተማ እስከ ወረዳ ባሉት መዋቅር ኤግዚቢሽንና ባዛር የማዘጋጀት ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። በየደረጃ የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ደረጃቸውን የጠበቁ እና ሳቢ በሆነ መልኩ ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ እንዲያስችል ራሱን የቻለ የኤግዚቢሽንና ባዛር አዘገጃጀት ጋይድ ላይን ተዘጋጅቷል። ሆኖም በገበያ ድጋፍ አሰጣጥ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች አበረታች ቢሆንም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ እና በቀጣይ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን ጥያቄ ሊመልስ በሚችል መልኩ በጥናት ላይ በተመረኮዘ መልኩ ተግባራትን የማከናወን ስራ መሰራት አለበት።

## 1.3 የአመራሩ፣ የፈፃሚው፣ የባለድርሻ አካላት እና የስራ ፈላጊዎች ሁኔታ እንደ መነሻ ፤

### 1.3.1 የዘርፉ አመራር ሁኔታ

የዘርፉ አመራር ማለት ከማዕከል እስከ ወረዳ ያለውን ተሿሚዎችን፣ ዳይሬክተሮችንና ቡድን መሪዎችን የሚመለከት ሲሆን የስራ እድል የመፍጠርና የዜጎች ተጠቃሚነት ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከለውጡ በፊት ከነበሩ አሰራሮች በተጨማሪ አዳዲስ አሰራሮችን እና ስልቶችን በመዘርጋት የከተማችንን ወጣቶች፣ ሴቶችና

ነዋሪዎችን ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ስራ ፈላጊዎች ያላቸውን የእውቀትና የጉልበት ካፒታል በመጠቀም መንግስት የሚያደርገውን ተጨማሪ ድጋፍ በመያዝ ወደ ስራ በመግባት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ህይወት እንዲለውጡ ለማድረግ አዳዲስ ሃሳቦችና አሰራሮችን በመዘርጋት የተጀመረውን ለውጥ ከዳር ለማድረስ እየሰራ ይገኛል።

የስራ እድል ፈጠራ ልማት ስራችን ውጤታማ የሚሆነው በዋናነት አመራሩ ቁርጠኝነት በተሞላበት ሁኔታ የዘርፉን ፈፃሚውንና ባድርሻ አካላት በተቀናጅና ውጤት በሚያመጣ መልኩ የድጋፍና ክትትል ስርአት ዘርግቶ አላሰራ ያሉ ማነቆዎችን ፈትሾ በፍጥነት መፍትሄ እየሰጠ ሲሄድና የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት ብልሹ አሰራሮች እንዳይፈጠሩ አሰራሮችን እየዘጋና እያሻሻለ ሲሄድና ተፈጥረው ሲገኙም የእርምት እርምጃ እየወሰደ ሲሄድ መሆኑ ግልፅ ነው።

በዚህም አመራሩ የዘርፉን ስራ ለማከናወንና ውጤት ለማምጣት እቅድ ከማዘጋጀት ጀምሮ እያንዳንዱ ፈፃሚ ሀይል የራሳቸውን ሚና መወጣት የሚያስችል እቅድ እንዲያዘጋጁ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከባለ ድርሻ ሴክተሮች ጋር በጋራ በመሆን ስራ ፈላጊ ዜጎችን መረጃ የማጥራት የመለየትና በመመዝገብ፣ ለስራ ፈላጊ ዜጎች በስራ ማማረጥና መጥላት ዙሪያ የግንዛቤ በማስጨበጥ የሙያ ክህሎት ስልጠና በቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ ተቋማት ገብተው እንዲሰለጥኑ በማድረግ፣ ከዩንቨርስቲና ቴ/ሙያ ተመርቀው የወጡ ሙህራንን በእድገት ተኮር ዘርፎች አደራጅቶ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረጉ፣ የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥም ስራዎቹ የደረሱበት በደረጃ በየጊዜው እየገመገመ ግብረመልስ መስጠትና አንድ ደረጃ ወርዶ በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ በስሩ ያሉትን ፈፃሚዎች ለማስገንዘብ የሚያደርገው ጥረት ከጊዜ ወደ እየተሻሻለ መጥቷል።

ይሁን እንጅ አመራሩ የዘርፉን ተልእኮ ለማሳካት እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም የስራ እድል ፈጠራ ስራችን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ካላደረገበት እንደማይሳካ በማመን የሚመለከታቸውን አካላት ሚናቸውን እንዲመጡ ማድረግ ላይ ሰፊ የሆነ ትኩተር ችግር የነበረበት ነው። በአመራሩ ዘንድ የተግባር አፈፃፀም ወጣ ገባነት የሚስተዋልበትና ስራውን በራስ አቅም ቀድሞ እየሰራ ከመሄድ ይልቅ የመጠበቅ ዝንባሌዎችም ይስተዋሉበታል። በስራ እድል ፈጠራችን ትኩረት ተደርጎ መሰራት የሚገባቸውን ጉዳዮች በመተው ምንም ይሁን ምንም እቅድን ለማሳካት ብቻ መንቀሳቀስ ማለትም የስራ የሚፈጠረውን ስራ እድል ጥራት ለማረጋገጥ የተዘረጉ መለኪያዎችን በተሟላ መንገድ አለመተግበር ችግሩ ሰፊ ነው። ይህም ደግሞ ወቅታዊ

ጉዳይን ለማለፍ ብቻ ታስቦ የሚሰራና የአመራር ባህሪን የማይገልፅ ጉዳይ ነው። የወጣቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ አለመስራትና በወጣቶች ዘንድ የሚስተዋለውን የስራ ማማረጥ አስተሳሰብን አለመታገል፣ ለክህሎት ስልጠና የሚውስዱትን ተከታትሎ እንዲደራጁና ወደ ስራ እንዲገቡ አለማድረግ፣ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ በሚፈለገው መንገድ በእቅድ እንዲመራ አለማድረግ፣ ስራ ፈጣሪ ተቋማት በእቅዳቸው መሰረት ተግባር ሳይፈፅሙና ሚናቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ አይቶ እንዳላየ በማለፍ ተግባሩን በትግል ሲመራ ያልነበረና በአድርባይነት በወጣቱ ተጠቃሚነት ላይ የሚደራደር ዝንባሌ ነበር።

ሌላው በአመራራችን የሚስተዋለው ውስንንት ችግሮችን በወቅቱ የመፍታታ አቅም ባለማዳበሩ በስራ ፈላጊው ዘንድ የሚነሱ ችግሮችን በመገንዘብ አስቸኮይ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ምክኒያቶችን በመደርደር ማመላለስና የቅሬታ ምንጭ መሆኑና ከችግር ጋር የመላመድ ዝንባሌዎችም ይሰተዋሉበታል። ከዚህ ባሻገር ስራና አሰራርን ከማጎልበትና ከማጠናከር አንፃር አመራራችን ተቆጥሮ የተሰጠውን ወቅታዊ ተልዕኮ ለማሳካት ከመንቀሳቀስ በዘለለ በመደበኛነት የዘርፉን ስትራቴጂክ ጉዳዮችን በተገቢው ለይቶ ያለመተግበር እና የተቀመጡ አሰራሮችን በጥብቅ ዲሲፕሊን ተከትሎ ያለመፈፀም ችግርበስፋት የሚስተዋልበት ነው። አመራራችን ጠንካራ የድጋና ክትትል ስረዓት በመዘርጋት የሚመራቸውን ፈፃሚዎች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተልዕኮዎቻቸውን እየተወጡ መሆኑን እየመዘኑ ካለመሄድ የተነሳ ደካማ አፈፃፀም ያላቸውን የመደገፍ እና የማብቃት ጉድለት እና የተሰጣቸውን ተግባር የሚያንጠባጥቡ ፈፃሚዎች እና አመራሮችን የተጠያቂነት አሠራር በመዘርጋት አለመጠየቅ ሰፋ ብሎ የሚስተዋል ችግር በመሆኑ አመራራችን የዕለት ተዕለት ስራ ላይ የማተኮር፣ በሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮችን ያለመለየትና ትኩረት ያለመስጠት ድክመቶች የሚታይበት በመሆኑ በቀጣይ ልናርመው ይገባል።

### 1.3.2 የፈፃሚው ነባራዊ ሁኔታ

በዘርፉ ያሉት ፈፃሚዎች ለእቅድ ስኬት የነበራቸው ድርሻ ከፍተኛ እንደነበር በግልፅ የሚታወቅ ሲሆን በተለይም ደግሞ ሞዴል ሆነው ስራዎችን ለመፈፀምና የተሰጣቸው ተልእኮ ለማሳካት የሚታትሩ ያሉ ሲሆን ሌሎች ተጨማሪ ስራዎች ሲሰጣቸውም ተግባራቱን ለማሳካት የሚያደርጉት ጥረት አበረታች ነው። ፈፃሚው ከአመራሩ ባልተናነሰ ሁኔታ በየቀጠናው በየመንደሩ በመግባት ትርፍ ሰዓትን ጭምር በመሰዋት ስራ አጦችን

በመለየት፣ መረጃ በማጥራት በመመዝገብ በማደራጀት ወደ ሥልጠና በማስገባት በመከታተልና በመደገፍ ጉልህ አስተዋጽኦ የማድረግ ጅማሮዎች ታይተዋል። ከነውስንነቱም ቢሆን የተፈጠሩ አደረጃጀቶች በመደበኛ የግንኙነት ጊዜያቸው ከዘርፍ ተልዕኮ አንፃር አጀንዳ ቀርጸው መወያየትና እርስ በርስ በመተጋገል፣ የለውጥ ስራዎችን በመተግበር አገልግሎቶችን በስታንዳርድ መሰረት እንዲፈፀሙ ጥረት የሚያደርጉ መኖሩ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከአመራሩ ጋር በመሆን ምላሽ እንዲያገኙ የማድረግ፣ በወረዳ ደረጃ ያለውን የግብአትና የቢሮ ምቹ አለመሆን ችግርን በመቋቋም ስራን ለመፈፀም የሚደረግ ጥረት በሠራተኛው ዘንድ እንደ ጥንካሬ ሊወሰድ የሚገባው ጉዳይ ነው።

ይሁን እንጂ ለዘርፍ ስራ ስኬት ፈፃሚዎቻችን የነበራቸው ሚና ከፍተኛ የነበረ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈፃሚዎቻችን ልክ እንደ አመራሩ ሁሉ መሰረታዊ የሆኑ ድክመቶች ይስተዋሉባቸዋል። ከሚታዩት ዋና ዋና ድክመቶች መካከል አንዱና ዋንኛው የአመለካከት ችግር ነው። ፈፃሚው የስራ ሰዓትን አክብሮ መገኘትና ሙሉ ጊዜን ለስራ ያለመስጠት፣ መደበኛ ስራን በራሱ በተሟላ አቅዶ ተግባሩን በተገቢው አውቆና ተቀናጅቶ በመፈፀም ራሱን በቻለ ሪፖርት ያለማድረግ ሁሉን ነገር ከሃላፊ የመጠበቅ፣ ተግባሩን በወቅቱ ሰርቶ ለመጨረስ አለመጣር፣ የሰራውን ስራ በተገቢው መረጃ አለመያዝ፣ የአገልጋይነት ስሜት ማነስ፣ ባለጉዳይን ማመናጨቅ፣ ማመላለስና ቶሎ ውሳኔ አለመስጠት፣ የዘርፉን የመረጃ ስረአት ለማዘመን የለማውን ሶፍት ዌር በእምነት ተቀብሎ አለመፈፀም፣ የለውጥ መሳሪያዎችን በእምነት ተቀብሎ መተግበርና ለውጥ ማምጣት ላይም ሰፊ ጉድለት ይስተዋላል። ከዚህም ባሻገር በስራ ላይ የሚቀርብበትን ቅሬታ በቅንነት ተቀብሎ ከመፍታት ይልቅ ውጫዊ የማድረግ ዝንባሌ የሚታይበት ሲሆን ከሌብነት አመለካከትና ተግባር ራሱን አፅድቶ ከመሄድ አንፃር የሚታዩ ጉድለቶች በመኖራቸውና የእርስ በእርስ ትግሉ የተቀዛቀዘ ስለሆነ ተልዕኮ ሲሠጠው እንዴት ማሳካት እችላለሁ ሳይሆን የሚያገኘውን የግል ጥቅም አስቀድሞ የማሰብ፣ ያልተገባ ጥቅም ከባለጉዳዮች ለማግኘት የመፈለግና የመቀበል ዝንባሌዎችም እየተስተዋሉበት ይገኛል። አብዛኞቹ የተሻለ ስነምግባር ያላቸው ቢሆኑም ይህ ችግር ያለባችን ታግሎ ከማረም ይልቅ በምንአገባኝ መንፈስ ስለሚያልፉት የሰራተኛውና የተቋሙ ስም በዚህ ችግር ሲጎድፍ ይሰማል። ይህ ችግር በዋንኛነት የሚስተዋለው ኢንተርፕራይዝ በማደራጀትና በስራና ገበያ ትስስር ተግባራት ላይ መሆኑ ተለይቷል።

ሌላ በፈጻሚዉ ዘንድ የሚስተዋለው መሰረታዊ ችግር የክህሎት ችግር ነው። ከዚህ አንፃር ፈፃሚው በዘርፉ ስትራቴጂና በሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች ውጤታማ አፈጻጸም ላይ በቂ ግንዛቤ ያለመያዝ ና የስራ እድል ፈጠራና የዜጎችን ተጠቃሚነት ግብ ለማሳካት ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ እቅድ በማዘጋጀትና በመተግበር ረገድ

በበቂ ክህሎት ከመስራት አንጻር ተጨባጭ ክፍተት መኖራቸውም ታይቷል። በየደረጃው የራሳቸዉን ፈጠራ በመጠቀም ለስራ ፈላጊዎች አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ወደ ስራ ለማስገባት የሚሰሩ ፈጻሚዎች ያሉ ቢሆንም ስራ ፈላጊው የሚፈልገውን አማራጭ በመለየት አስፈላጊዉን ድጋፍ በመስጠቱ ሂደት የሚታይ የክህሎት ክፍተት አለ።

በሌላ በኩል የዘርፉ ስራዎች በበቂ እውቀት ለማከናወን የመረጃ ስርዓቱ ወጥነት ያለው እንዲሆን በማድረግ ቅብብሎሹ ጥራት ያለዉና ወቅታዊ እንዲሆን በቀጣይነት እንዲፈጸም ማድረግ ያስፈልጋል። የዘርፉ ፈጻሚዎችም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ተአማኒነት ያለዉ መረጃ ጥራትና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ እንዲላክ ከማድረግ አንጻር የበኩላቸዉን ሚና እንዲወጡ የሚጠበቅ ቢሆንም የሚተላለፍው መረጃ ጥራቱን ያልጠበቀ የመረጃ አያያዝና በወቅቱ ያለመላክ የክህሎት ችግር ጎልቶ ታይቷል።

ስራ ፈላጊዎች የስራ ጊዜ ብክነትና እንግልት ለማስወገድ የተቀናጀና ቀልጣፋ አገልግሎትን በአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ሁሉንም አይነት አገልግሎቶችን በሚፈለገዉ ደረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ። ቢሆንም በአንድ ማእከል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ፈጻሚዉ አላማዉንና ጠቀሜታዉን ተረድቶ ለተገልጋዩ ተገቢዉን መረጃና ግንዛቤ አለመስጠት፣ በአሰራር ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ስራዎችን የመገፋፋት ዝንባሌ ታይቷል። በአንድ ማዕከሉ አደረጃጀትና አሰራር ላይ የግንዛቤ እጥረት ሰፊ በመሆኑ ጊዜ ሳይወሰድ በቀጣይ ትኩረት በመስጠት መፍታት ያስፈልጋል። በአጠቃላይ በዘርፉ የተሰማራው ከጊዜ ወደ ጊዜ ተግባራን በውጤታማነት ለመፈፀም የሚደረግ ጥረት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በዘርፉ ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር ግን በርካታ ያልተሻገርናቸውና ውስብስብ ችግሮች ያሉ መሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ ጊዜ ከችግሩ ለመውጣት መስራት ይኖርብናል።

### 1.3.2 የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እንቅስቃሴ እንደ መነሻ

ቢሯችን ለወጣቶችና ለሴቶች እንዲሁም ለነዋሪዎች ቋሚና ጊዚያዊ የስራ እድል የሚፈጥር ተቋም ሲሆን ይህን ተግባር በአግባቡ በተያዘለት ጊዜ ለማከናወን የባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ነው። በዚሁ መሰረት የስራ እድል ፈጣሪ ተቋማት በቅንጅት ስራ ሊፈጥሩ የሚያስችሉ ዘርፎችን በመለየትና የተቀናጀ የጋራ እቅድ በማዘጋጀት ወጣቱን ወደ ስራ ለማስገባት ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። አጠቃላይ አፈጻጸሙንም በየደረጃው በተቋቋሙ የስራ እድል ፈጠራ ምክር ቤቶችና አስተግባሪ ኮሚቴዎች እየተገመገመ የጋራ አቅጣጫ እየተሰጠበት እንዲሄድ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ምንም እንኳን ለስራው ትኩረት

ሰጥተው በባለቤትነትና በተነሳሽነት የስራ እድል ፈጠራ ስራውን ለመምራት የሞከሩ ሴክተሮች የነበሩ ቢሆንም በዚያው ልክ ደግሞ የስራ እድል ፈጠራ ስራው ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ብቻ ትዝ የሚላቸው አንዳንድ ተቋማትም ተስተውለዋል። ስለሆነም የስራ እድል ፈጠራ ስራችን የአንድ ሴክተር መስሪያ ቤት ተልእኮ ብቻ አለመሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱ መስሪያ ቤት በሚያከናውናቸው ተልእኮዎች ሁሉ የስራ እድል ፈጠራ ስራው ታሳቢ በማድረግ ለበርካታ ዜጎች ስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ግቦችን ቀርጸው ለተግባራዊነታቸው ያለማንም ቀስቃሽ በሙሉ ትኩረት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ይገባል።

### 1.3.3 የሥራ ፈላጊ ወጣቶችና ሴቶች የሚገኙበትን ሁኔታ እንደ መነሻ ፤

በከተማችን አዲስ አበባ በርካታ የሥራ ፈላጊ ቁጥር የሚገኝ ሲሆን በተለይም ከተማዋ ካላት ያሳቢነት ባህሪ ማለትም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና መሰረተ ልማት እድገት ምክኒያት ከክልሎች ወደ ከተማችን የሚገባው ስራ ፈላጊ ኃይል ከግዜ ወደ ግዜ ቁጥሩ እየጨመረ በመሆኑ የሥራ እጥነት ችግርን ለመቅረፍ የሚሠራውን ሥራ እያከበደው ይገኛል። በከተማችን የሚገኙ ወጣቶች መንግስት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በማየት በተለያ መስኮች ተደራጅተው ለመስራት መነሳሳት አሳይተዋል። በፊት የነበረው በመንግሥት መስሪያ ቤት ብቻ ተቀጥረው ለመስራት የመፈለግ አዝማሚያ መጠነኛ ለውጦች በማሳየት በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ በተመረጡ ዘርፎች ማለትም በማኑፋክቸሪንግ፣ በከተማ ግብርና በዳቦ መሸጥና በመሰሰሉት ዘርፎች ወደ ስራ በመግባት ላይ ይገኛሉ። ወደ ስራ የገቡ ወጣቶችና ሴቶችም የሚደረግላቸውን መንግስታዊ ድጋፍ ወደ ተጨባጭ ተግባር በመቀየር ውጤታማነታቸውን እያረጋገጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግና በገበያ ተወዳዳሪ የመሆን አስተሳሰብ በመኖሩ የካፒታል አቅም ማዳበር እየተቻለ ነው።

ይህ በጐ ጅምር ቢኖርም አሁንም አብዛኛው ወጣት ጉልበት ተኮር በሆኑ ስራዎች ለመሳተፍ ያለው ፍላጐት ዝቅተኛ ነው። የከተማችን ወጣቶች ቀለል ወዳሉና በአቋራጭ የተሻለ ገቢ የሚያስገኙት ስራዎች ለአብነትም የመኪና እጥበት የሚስራበት ክፍት ቦታ ለማግኘት መረባረብ ይታያል። በሌላም በኩል ወጣት በራሳቸው ስራ ለመፍጠር ያላቸው ተነሳሽነት ደካማ ከመሆኑም በላይ ሁሉን ነገር ከመንግሥት የመጠበቅና የማማረጥ እንዲሁም እነሱ በፈለጉት ፍጥነት ስራው አልገኝ ሲል ደግሞ ቶሎ ተስፋ መቁረጥና ማማረር ይታያል። በዚህም ትመዘግቡናላችሁ እንጂ ሥራ አታስገቡንም ሰልችቶናል፣ ትናገራላችሁ ግን አትፈጽሙም፣ ወደ ወረዳ ስንሄድ እያስተናግዱንም የሚሉና ሌሎቹንም ጉዳዮች የሚያነሱ በርካቶች ያሉ ሲሆን በመንግሥት በኩል ስለሚደረገው የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴ ግንዛቤ የሌላቸውና በየጥጋጥጉ ተቀምጠው የሚውሉ

በተመሳሳይ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ስለሆነም የስራ ፈላጊዎች ወላጆችን በማሳተፍ የለውጡ አጋዥ በመሆን እንዲሳተፉና በከተማችን ለሚገኙ ዜጎች ተጨባጭ ስራ በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ለነገ የሚባል ጉዳይ ባለመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሃላፊነትና ውግንና መፈፀም ይኖርብናል።

### 1.4 ጠንካራ ጎኖች እና ደካማ ጎኖች እንደ መነሻ፤

## ጠንካራ ጎኖች

- ሥራው/መዋቅሩ ከሚፈልገው አንፃር ሊያሠራ የሚችል የትምህርት ዝግጅት፣ የተለያየ ልምድ ያለው የሰው ኃይል መኖሩ በጠንካራ ጎንነት ተለይቷል።
- ከማዕከል እስከ ወረዳ ተናባቢነት ያለውን መዋቅራዊ አደረጃጀት ለመፍጠር ጥረት መደረጉ፣ ዘርፉን በተመለከተ የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶች በማስተባበር እየተሠራ መሆኑ፤ ኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ድጋፎች እንዲያገኙ መደረጉ፤ ለኢንተርፕራይዞች ምቹ የስራ አካባቢ ከመፍጠር አንፃር የተሰሩ ውስንስራዎች መኖራቸው፤ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉ፤ በአንድ ማዕከል አገልግሎት የተቀናጀ አገልግሎት ለመስጠት ጅምር ስራ መኖሩ ከአደረጃጀትና አሰራር አንጻር በጠንካራ ጎንነት ተለይተው ቀርበዋል።
- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በሁሉም ወረዳዎች ተከፍተው እየሰሩ መሆኑ፤ ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጋቸው፤
- ኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ድጋፎችን እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑ፤
- ከፋይናንስና ግብዓት አቅርቦት አቅም አንፃር እንደ ጠንካራ ጎን ሊወሰዱ ከሚችሉ ነጥቦች መካከል ለቢሮው ሥራ ማስፈጸሚያ የሚመደበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ እና ለኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ካፒታልና የማሽን ብድር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት (አዲስ ብድር እና አዲስ ካፒታል ዕቃ አቅርቦት) እንዲቋቋሙ መደረጉ የሚጠቀሱ ናቸው።
- የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማለትም የተቀናጀ የአንድ ማዕከል የመረጃ ስርዓት መዘርጋቱ፣ የኤምኤስኢ ዘን፣ የወረዳ ኔት፣ ለንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የንግድ ሲስተምን መጠቀም መቻሉ፣ የኢንፎርሜሽናል ሞባይል አፕሊኬሽን መልማቱ፣ ለደንበኞች መረጃ መስጫ እና የተገልጋዮችንቅሬታን በድምፅ ለመቀበል የሚረዳ ቴክኖሎጂ መተከሉ፣ የስራ ፈላጊ ዜጎችን በሞባይል አፕሊኬሽን መመዝገብ መጀመሩ ጅምር ስራዎች መኖራቸው ጠንካራ ጎኖች መሆናቸው ታይቷል።

## ደካማ ጎን

- አመራሩም ሆነ ባለሙያው ዘርፉ በሚጠይቀው ስልጠና ያልታገዘ፤ የክህሎት ክፍተት ያለበት፤ የእርስ በርስ ግንኙነቱ የላላ ፤ ሥራዎችን በቡድን የመሥራት ባህሉ ዝቅተኛ መሆኑ ፤ ለተገልጋይ የተሟላና የተቀላጠፈ አገልግሎት አለመስጠት፣ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ ወጪና ጥራት አለማጠናቀቅ ፤ የአመራር በአጭር ጊዜ መለዋወጥ ፤ ልምድ ያለው ባለሙያ ከስራ መልቀቅ፤ ተቋማዊ የአቅም ውስንነት (ስትራቴጂውን ተረድቶ ተግባር ላይ የማዋል ክፍተት፤ ቴክኖሎጂ መቅዳትና መተግበር፤ አዳዲስ አስተሳሰቦችና አሰራሮች አለመተግበር፣ የጥናት ግኝቶች የመቀበልና የመተግበር)፤ የባለሙያ እና የአመራር ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት ዝቅተኛ መሆን የሰው ኃይልን በተመለከተ በድክመት ተለይተዋል።
- በየጊዜው የሚለዋወጥና ያልተረጋጋ መዋቅር መኖሩ እና በዚህ ላይ የሚነሱ የሰራተኞች ቅሬታዎችን አለመፍታት፤ ተቋማዊ የመወሰን አቅም ውስንነት (የተርንኪ ፕሮጀክትን ለማስተዳደር፤ ያስገኘውን ፋይዳ በጥናት መለየት አለመቻል፤ በታዩ ችግሮች ላይ ማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ፤ በውስጥም ሆነ በውጪ ቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር፤ ቴክኖሎጂ ለመምረጥ የቅድመ እና ድህረ አዋጪነት ጥናት አለማካሄድ፤ አጠቃላይ ስራዎችን በጥናትና ምርምር የተደገፉ አለማድረግ ፤ የኢንኩቤሽን ማዕከል በሚፈለገው ልክ አደራጅቶ አለመጠቀም)፤ የተጠናከረ የቡድን ስራዎች ለመሥራት የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ የውስጥ ባለሙያዎችን አቅም የመጠቀም ክፍተት፤ የኢንተርፕራይዞችን ተጨባጭ ችግር በለየ ሁኔታ ድጋፍ የመስጠት ችግር፤ የእውቅናና ማበረታታቻ ስርዓት አለመዘርጋት፣ ለባለጉዳዮች ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት አለመቻል፤ መንግስታዊ ድጋፎችን በተሟላና በተቀናጀ አሰራር መስጠት አለመቻሉ፤ ስራዎችን በስታንዳርድ መሰረት አለመስራት፤ አምራች ኢንተርፕራይዞች በአገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ፣ ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አሠራር አለመዘርጋቱ፤ ለምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎች በስራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ካሳ ክፍያ የሚያገኙበት አሰራር አለመኖሩ፣ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍና ለማሸጋገር ግልጽ አሰራር አለመኖሩ፤ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የተለየ የድጋፍ አግባብ አለመኖር በአደረጃጀትና አሰራር ላይ የታዩ ክፍተቶች ናቸው።
- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ለተገልጋዮች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ አለመደራጀቱ ፤ ምቹ የስራ አካባቢ አለመደራጀት፣ በጥሪት ማፍሪያ ስራ ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ዕድገት ተኮር ዘርፍ እንዲያድጉ አለመደረጉ፣ መልካም ተሞክሮዎችን ለመቀመር እናለመተግበር የሚደረግ ጥረት ውስንነት ያለበት መሆኑ፤ የተለየ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው

ዜጎች /አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶችና የኤች.አይ.ቪ ህመምተኞች/ በጥናትላይ የተደገፈ አገልግሎት ለመስጠት የተቋሙየመተግበር አቅም ውስንነት ፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በጥናት በመለየት የመፍታት ውስንነት፤ አገልግሎቶችን በተቀመጠዉ ስታንዳርድ መሰረት አለመስጠት፣ ለተገልጋዮች በሚሰጡ አገልግሎቶችዙሪያ ለደንበኞች ግንዛቤ መፍጠር አለመቻል፣ እንዲሁም ለኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታዎች አቅርቦት የመሰረተ ልማት ማሟላት አለመቻሉ በዋናነት በመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ክፍተት ሆነው ተለይተዋል።

- የቢሮ ቁሳቁስ በሚጠበቀው ደረጃ ማሟላት አለመቻሉ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አለመሟላት፣ በጀትን በአግባቡ እና በዕቅድ መሠረት አለመጠቀም፣ግዥዎች በዕቅድ መሠረት (ጊዜ እና ጥራት) አለመፈፀማቸው፣ በቂ ተሸከርካሪዎች አለመኖር እና ቢሆኑ ያሉትም በእርጅናና በብልሽት ምክንያት ተፈላጊውን አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸው፣ የተሸከርካሪ ስምሪት ስርዓቱ ችግር ያለበት መሆኑ፣ የመስሪያ ቦታዎችን በወቅቱ ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ የማድረግክፍተትመኖሩ፣ የሥልጠናበጀት በሌላ አካል እንዲመራ መደረጉ፤ ለኢንተርፕራይዞች በቂ የመስሪያ ቦታ ማልማትና ማቅረብ አለመቻል ከፋይናንስና ግብዓት አቅርቦት አኳያ በድክመት የተለዩ ጉዳዮች ናቸው።
- ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አመራሩና ፈጻሚው አካል በአመለካከት እና በክህሎት ክፍተት ያላቸው መሆኑ፣ የሲስተም መቆራረጥ መኖሩ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርጭት /በድረ ገፅ፣ በፌስ ቡክ፣ በቋሚ መፅሄቶች፣ ጋዜጣዎች/ ተቋማዊ አቅም አናሳ መሆን፣ የመረጃ እና ሪፖርት ጥራት ችግር እና ወቅታዊ አለመሆን ከቴክኖሎጂ አንጻር በድክመት የተለዩ ጉዳዮች ናቸው።

## 1.5 መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች እንደመነሻ

### መልካም አጋጣሚዎች

- ዘርፉን ለማሳደግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፆ ተግባራዊ መደረጉ፤ እና የስራ ዕድል ፈጠራና የትምህርት ስልጠና ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱ፤አዳዲስ አሠራሮችና ተቋማዊ ሪፎርሞች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፤ ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት መኖሩና ከተማዋ የአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ መሆኗ፤
- የኢንዲስትሪ ፓርኮች መስፋፋትና ለኢንተርፕሩነር ኢንኩቤሽን ማዕከልነት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መኖሩ፣የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ባለሀብቶች

ለማስተላለፍ ስራ መጀመሩ፤ የኢንዱስትሪ ልማትን በማሳደግ ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር የሚያስችሉ አማራጭ ፀጋዎች መኖራቸውና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ ብድሮችና እርዳታዎች መኖራቸው፤የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትና የባንኮች መስፋፋት፤ከተማ አስተዳደሩ ለወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት የተዘዋዋሪ ብድር ማመቻቸቱ፣ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ትኩረት መሰጠቱና የክላስተር ማዕከላት የማልማት ፍላጎት መኖሩ፣ሀገራችን ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) ተመራጭ መሆኗናኤክስፖርትን የሚያበረታታ ፖሊሲ መኖሩ፤የኃይል አቅርቦት መሻሻል ለኢንዱስትሪ መስፋፋት የሚኖረው በጎ አስተዋጽዖ፤

- የምርምርና ስርፀት ተቋማት እና የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ፍላጎትና አቅም እያደገ መምጣቱ፤ በሀገራችን የዲጂታል ማርኬቲንግ እየተስፋፋ መምጣቱ፣ የመገናኛ ብዙሃንና የማህበራዊ ሚዲያ ብዛትና ስፋት መጨመሩ፣ የኢ-ሰርቪስ እና ሞባይል ስልክ አገልግሎት ለመስጠት ጅምሮች መኖሩ ፤
- የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ፖለሲ ከዘርፉ የልማት ስራዎች ጋር ቀጥታ ተዛማጅ እና ተመጋጋቢ መሆኑ፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን የመደበኛ ስራቸው አካል አድርገው መጀመራቸው፤

## ስጋት

- በከተማ አስተዳደሩና በፌዴራል ደረጃ ያለው አደረጃጀትና አሰራር የተናበበና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚስችል አለመሆኑ፤ ያልተረጋጋ እና ጥናትን መሰረት ያላደረገ በፍጥነት የሚለዋወጥ የአደረጃጀት መዋቅር) መኖር፤ የመልካም አስተዳደር ጉድለት (የሌብነትና ብልሹ አሠራር በአመለካከትም ሆነ በተግባር ያልተቀረፈ መሆኑ ፤ ግልፀኝነት እና ተጠያቂነት አለመስፈን) የሀገሪቱ የፀጥታ ሁኔታ አለመረጋጋት በኢንቨስትመንትና በስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ተፅዕኖ፤ በዘርፉን ለመደገፍና ውጤታማ ለማድረግ በፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኝነት ተነሳሽነትና ፍላጎት ያለመኖር፤
- ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም፤ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት አሰራር ቀልጣፋና ወቅታዊ አለመሆን፣ የኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ፍላጎት በሚፈለገው ደረጃ አለመሟላት፤ ኢንተርፕራይዞች በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ በሚፈለገው ደረጃ በዋጋ ፤ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ አለመሆናቸው፣ ከትምህርትና ስልጠና የሚወጡ ሰልጣኞች ቁጥር ከፍተኛ መሆን፤ በኢንዱስትሪዎች ሰፊ የስራ ትስስር አለመፈጠርና የፍላጎት ማጣት፤የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለሃገራችን ፈተና መሆኑ፤ ኮቪድ-

19 በዝቅተኛ ኑሮ ላይ ያለውን ማህበረሰብ የመግዛት አቅም በማዳከምና በለጋሽ ሀገሮችም ላይ በሚፈጥረው ተጽኖ ምክንያት የሥራ እድል ፈጠራ ስራዎችና የኢንተርፕራይዞችን እድገት ሊጎዳ የሚችል መሆኑ፤ ስራ ፈላጊዎችና አንቀሳቃሾች በመንግስታዊ ድጋፎች ላይ ጥገኛ መሆን፤ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ክላስተር ማዕከላት ለማልማት የሚያስችል መሬት አቅርቦት ውስንነት መኖሩና ትኩረት አለመሰጠቱ፣ዋስትና ማስያዝ ለማይችሉ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችና ኢንተርፕሩነሮች የዋስትና ፈንድ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤ የማሽነሪ ሊዝ እና የመስሪያ ካፒታል አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ጎታች የሆኑ መስፈርቶች መኖርና በዘርፉ በቂ የሀገር ውስጥ ማሽነሪ አምራቾች አለመኖራቸው፤ በህገወጥ ንግድ መስፋፋት ምክንያት የአምራች ኢንተርፕራይዞች ገበያ እጥረት መኖር፤

- ከትምህርት ተቋማት የሚወጡ ምሩቃን ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የስራ ፈጣሪነት አሰተሳሰብና ክህሎት ይዞ አለመገኘት፣ ስራ ማማረጥ እና የስራ ዲስፕሊን አለመዳበር፣
- ከኢኮኖሚ ጋር ያልተጣጣመ የህዝብ ዕድገት መጨመር ፤ በማህብረሰቡ የኢንተርፕራይዝ ምርቶችን የመጠቀም ባህልና በምርቱ ጥራት ላይ ያለው መተማመን ዝቅተኛ መሆኑ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ህብረተሰቡ ቅንጅት አለመኖር፤ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ በአቋራጭ ለመበልጸግ የመፈለግ ዝንባሌዎችና አስተሳሰቦች እያደጉ መምጣት፤
- ከተለመደው አሠራር ለመላቀቅ አለመፈለግ፣ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ያለው አመለካከትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት በማሻሻል እና በመፍጠር ጥቅም ላይ ለማዋል የእውቀትና የክህሎት ችግር መኖሩ፣ በአግባቡ የመጠቀም ችግር መኖር፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ደካማ መሆን፤ ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሳደግና ለመጠቅም የሚያስችል ስርአት ያለመዘርጋቱ፣

## 3. ራዕይ፣ ተልዕኮ፤ እሴት

### ራዕይ

በ2022 ሰፊ የስራ እድል የፈጠሩ ተወዳዳሪና ለኢንዱስትሪ ዕድገት መሰረት የጣሉ ኢንተርፕራይዞች ከተስፋፋባቸው የአፍሪካ ከተሞች ቀዳሚ ሆኖ ማየት።

**ተልዕኮ**

ከዘርፉ ልማት አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በዘርፉ ስትራቴጂ የተቀመጡ መንግስታዊ የድጋፍ ማዕቀፎችን በመዘርጋት ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ የተቀናጀ አገልግሎት በመስጠት የተደረገላቸውን ድጋፍ በመጠቀም ለራሳቸውና ለሌሎች ስራ ፈላጊ ዜጎች አስተማማኝ የስራ ዕድል የፈጠሩና ለኢንዱስትሪ ልማቱ መሰረት የሚጥሉ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጣ በማስቻል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ።

**እሴቶች**

- ስራ ፈጣሪነትን ማበረታታት፣
- ፍትሃዊ የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣
- ግልጽና አሳታፊ ተጠያቂነት ፤
- የላቀ አገልግሎት መስጠት፣
- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት፣
- ሁልጊዜም ከተግባር መማር ፤
- ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማረጋገጥ፣

## 6. የቁልፍ ተግባሩ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት

**ግብ 1፡- በዘርፉ በየደረጃው የሚገኘው 392 አመራርና 2500 ፈጻሚ አቅም በመገንባት መዋቅሩ እንዲጠናከርና የባለድርሻ ተሳትፎን በማጎልበት ተልዕኮውን በውጤታማነት እንዲወጣ ይደረጋል።**

ተግባር 1፡- የዘርፉን የ2013 በጀት አመት መሪ ዕቅድ በማዘጋጀት ከማዕከል እስከ ታችኛው መዋቅር እንዲናበብ ማድረግ፣

ተግባር 2፡- የተዘጋጁትን ዕቅዶች አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የሚገኘው አካል ገምግሞ ግብረ-መልስ እንዲሰጥ ማድረግ፣

ተግባር 3፡- ለ392 በየደረጃው ለሚገኙ የዘርፉ አመራርና 2500 ፈፃሚዎች የ2012 አፈፃፀም ግምገማና የ2013 ዕቅድ ቀርቦ ውይይት እንዲካሄድበት ማድረግ፣

ተግባር 4፦ በየደረጃው ለሚገኙ 300 የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጎልበትና አቅማቸውን ለመጠቀም በአፈፃፀም ግምገማ፣ እቅድ ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣

ተግባር 5፦ ለ392 የዘርፉ አመራሮችና ለ2500 ፈፃሚዎች በዘርፉ ተልዕኮ፣ ስትራቴጂና በአዲሱ መዋቅራዊ አደረጃጀት ላይ ስልጠና በመስጠት ስራቸውን በዕውቀት እንዲመሩ ማድረግ፣

ተግባር 6፦ የአመራሩና ፈፃሚዎች አቅም ለመገንባት የሚያስችል የፍላጎት ዳሰሳና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች መስጠት፣

**ግብ 2፦ በየደረጃው የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመለየት ደረጃ በደረጃ እንዲፈቱ በማድረግ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፦ በዘርፉ በየደረጃው ያልተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለይቶ የአፈታት ስልቱን በሚያሳይ አግባብ ራሱን የቻለ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፦ በዕቅዱ መሰረት ተግባራት እየተፈጸሙ መሆኑን በየጊዜው በአመራር እየተገመገመ እንዲሄድ ማድረግ፣

ተግባር 3፦ በዘርፉ የሚሰጠው አገልግሎቶች የተቀመለጠላቸውን የአገልግሎት ተደራሽነት፣ ስታንዳርድና ጥራት ጠብቆ እንዲሰጥ ማድረግ፣

**ግብ 3፦ በዘርፉ የሚታየውን በአቋራጭና ያለአግባብ የመጠቀም ፍላጎቶችና ተግባራትን የተደራጀ ትግል እንዲዳከምና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፦ በዘርፉ በየደረጃው ለብልሹ አሰራሮች ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን ለይቶ የማስተካከልና አሰራሩን የማዘመን ስራ መስራት፣

ተግባር 2፦ የዘርፉ አመራርና ፈጻሚ ከሌብነት አስተሳሰብና ተግባር ነጻ እንዲሆን ተቋማዊ እሴቶችን ማስረፅና ሙያዊ ስነ-ምግባር እንዲላበስ የአመለካከት ቀረጻ ስራ አጠናክሮ መፈጸም፣

ተግባር 3፡- በየደረጃው በዘርፉ የሚሰጡ ድጋፎች ፍትሃዊና ከብልሹ አሰራር የጸዱ እንዲሆኑ ማድረግ፣ አፈጻጸሙን ኢንስፔክትና ኦዲት እያደረጉ ክፍተቶች ሲገኙ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

ተግባር 4፡- በየደረጃው የሚዘጋጁና የሚላኩ ሪፖርቶች ተዓማኒና ከውሸት ሪፖርት የጸዱ መሆናቸውን በክትትልና ድጋፍ እያረጋገጡ መሄድና ችግር ያለባቸውን አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፣

ተግባር 5፡- በዘርፉ የሚስተዋሉ የሌብነትና እላፊ ተጠቃሚነት አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ለማዳከም የባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችል የጋራ ስራ መስራት፣

**ግብ 4፡- የለውጥ ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ በዘመናዊ አሠራር በማስደገፍና በመተግበር የተገልጋይ እርካታ እንዲያድግ ይደረጋል።**

ተግባር 1፡- የለውጥ ስራዎች የሚመሩበት እራሱን የቻለ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ፣

ተግባር 2፡- የሚዛናዊ ሥራ አመራርና ውጤት ተኮር ስርዓትን በተሻሻለው አደረጃጀት መሠረት ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ ለእያንዳንዱ የስራ ክፍልና ለእያንዳንዱ ፈፃሚ ካስኬድ ተደርጎ እንዲደርሰው ማድረግ፣

ተግባር 3፡- በየደረጃው ሁሉም ስራዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እየተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥና ከስታንዳርድ በላይ፣ በስታንዳርዱና ከስታንዳርድ በታች የሚፈፅሙ የስራ ክፍሎችና ባለሙያዎች እየተለዩ እንዲሄዱ ማድረግ፣

ተግባር 4፡- የለውጥ ቡድኖችና የሞርኒግ ብሪፊንግ አደረጃጀት በመደበኛ የግንኙነት ጊዜያቸው እየተገናኙ ተልእኳቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣

ተግባር 5፡- በዘርፉ የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በሁሉም ወረዳዎች ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥና ሠራተኛውን በማሠልጠን የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን ማጠናከር፣ የሪፓርት አግባቡም በሲስተም ብቻ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 6፦ የስራ አፈፃፀም ጥራትና የውጤት ምዘና ሂደት ላይ ግልፅ አሰራር በመዘርጋት ምዘናውን ማካሄድና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየትና በማስፋት እውቅና መስጠት፣

**ግብ 5፦ ልማታዊ አስተሳሰብና ተግባራትን ለማጎልበት የሚያስችል ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥና የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ይሰራሉ።**

ተግባር 1፦ የህዝብ ግንኙነት ስራው እራሱን በቻለ እቅድ ተዘጋጅቶለት በተደራጀ መልኩ እንዲመራ ማድረግ፣

ተግባር 2፦ የህዝብ ግንኙነት ሥራችን (ሁሉንም አማራጮች የኤሌክትሮኒክስ፣ የህትመት፣ ሶሻል ሚዲያንና ሌሎችንም) እንዲጠቀም ማድረግ፣

ተግባር 3፦ ስራን የመናቅ፣ የጠባቂነት፣ በአቋራጭ ለመክበር መሞከር፣ የስራ ባህል አለመጠናከር እና መሰል አመለካከቶችን የማስተካከል ስራን መስራት፣

ተግባር 4፦ የህዝብ ግንኙነት ስራችን በተግባር ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ የተሻሉ ተሞክሮዎችን የሚያሰፋ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 5፡ ሁሉም በየደረጃው የሚገኝ አመራር የህዝብ ግንኙነት ሥራውን በባለቤትነት ይዞት እንዲተገብረው ማድረግ፣

## 7. ዓበይት ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት፤

### ግብ 1 ፦ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን በግብአትና በሰው ሃይል በማጠናከር በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዘመናዊ፣ ተደራሽ እና ምቹ ማድረግ ተችሏል።

ተግባር 1፦ግንባታቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ የ18 አንድ ማእከላት ግንባታ በማጠናቀቅ አገልግሎት እንዲጀምሩ ማድረግ፣

ተግባር 2፦ በያዝነው በጀት ዓመት የ30 አንድ ማእከላት ግንባታ በማስጀመር 50% ማድረስ፣

ተግባር 3፦ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎቹ የተጓደሉ ግብአቶች ተለይተው 70 በመቶ እንዲሟላ ማድረግ፤

ተግባር 4፡- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት በ121ዱም ወረዳዎች እንዲደራጅ በማድረግ የተጎደሉትን 70 በሞቶ በሰዉ ሃይል ማሟላት፤

ተግባር 5፡- አዲስ እየለማ ያለውን የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ሲስተም በማጠናቀቅ በ60 አንድ ማእከላት አገልግሎቱን ማስጀመር፤

ተግባር 6፡- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአንድ ማዕከል ስታንዳርድ መሰረት እንዲፈፀም ማድረግ፣

ተግባር 7፡- ተጠናክረው ወደ ስራ ከገቡ የአንድ ማዕከል ጣቢያዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 30 ሞዴል የአንድ ማዕከል ጣቢያዎችን መፍጠር፤

### ግብ 2፡- የንግድ ህጉን መሰረት በማድረግ 95,318 አንቀሳቃሾች በ19,988 ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ማድረግ፤

ተግባር 1፡- በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ እና በደንበኛ አያያዝ (Service delivery & Custmer Handling) ዙሪያ ለቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር 2፡- የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን በጥናት በመለየት ይተገበራል፤

ተግባር 3፡- በሁሉም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ በማጠናከር በስታንዳርድ መሠረት የተሟላ አገልግሎት መስጠቱን ማረጋገጥ፣

ተግባር 4፡- ኢንተርፕራይዞች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ህጋዊ ሰውነት ማገኘታቸውን ማረጋገጥ፣

ተግባር 5፡- በአንድ ማዕከል ለተመደቡ 947 አዳዲስ ፈጻሚዎች በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሠጣጥ፣ በማስፈጸሚያ መመሪያዎች እና በደንበኛ አያያዝ ላይ ስልጠና መስጠት፣

### ግብ 3፡- 280,000 የሚሆኑ ተገልጋዮች በ121 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፣

**ተግባር 1፡-** በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥና አተገባበር ዙሪያ ለዘርፉ ባለሙያዎች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት፤

**ተግባር 2፡ 280,000** ለሚሆኑ ዩኒቨርሲቲ፣ የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን እና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች የመረጃ፣ ምክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ አገልግሎት በመስጠት ምዝገባ ማካሄድ፤

**ተግባር 3**፡- በንግድ ህጉ መሰረት ለ**95,318** ሰዎች የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት ለሚደራጁ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰርቲፊኬት መስጠት፣

**ተግባር 4፡ 19,988** የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች በግል፣ በህብረት ሽርክና ማህበርና በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በማደራጀት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እንዲያወጡ ማድረግ፤

**ተግባር 5**፡- ለኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ድጋፎችን በአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጠቱን በድጋፍና ክትትል እንዲሁም በዳሰሳ ጥናት ማረጋገጥ፣

## ግብ 4 ፡- በቴክኖሎጂ የተደገፈ የተደራጀ ፤ የተተነተነና የተሰራጨ የስራ ፈላጊዎችና ኢንተርፕራይዞች መረጃ ማዘጋጀት ተችሏል፤

ተግባር 1 ፡- በአንድ ማእከላቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራቱን የጠበቀ መረጃ እንዲደራጅ ማድረግ ፤

ተግባር 2፡- በአንድ ማዕከል ህጋዊነትን ለማስፈን የሚሰጡ አገልግሎቶች መረጃ ማደራጀትና የመተንተን ስራ ይሰራል፣

ተግባር 3፡- በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች መረጃ የማደራጀትና የመተንተን ስራ ይሰራል፣

## ግብ 5 ፡- ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች (ለሴቶች፤ ለወጣቶች፤ ለአካል ጉዳተኞች፤ ኤችአይቪ ኤድስ በደማቸዉ ለሚገኝ ዜጎች) ተሳታፊና ተጠቃሚ እንሆኑ ተደርጓል፣

ተግባር 1፡- የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከ35 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማድረስ ፤

ተግባር 2 ፡- የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት 70 በመቶ ማድረስ፤

ተግባር 3 ፡- 200 አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ፤

ተግባር 4 ፡- 50 ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለ ተጠቃሚ ማድረግ፤

**8. የአፈጻጸም አቅጣጫ፤**

5.1. የምናከናውናቸውን ተግባራት ተቋማዊ በሆነና የተፈጠሩ አደረጃጀቶችን በቀጣይነት ወደ ተጨባጭ ተግባር በማስገባት የመፈፀም አቅማችንን ማጎልበት እንደ ዋነኛ አቅጣጫ ይዘን እንሰራለን፣

5.2. የአገልግሎት አሰጣጣችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ግለጽ፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በማድረግ የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት በማርካት መልካም አስተዳደርን በሚያሰፍን ሁኔታ በትጋት ይሰራል፣

5.3. ተግባሮቻችን በሙሉ ልማታዊ አስተሳሰብን በሚያጎለብትና ሌብነትን በሚያዳክም መንገድ እንዲፈጸሙ የማድረግ አቅጣጫን አንከተላለን።

5.4. ተግባሮቻችን አሳታፊ፣ ግልጽና ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ እንዲፈጸሙና የህዝብ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አቅጣጫ እንዲፈጽሙ እንሰራለን።

5.5. ተግባሮቻችን በሙሉ በባለድርሻ አካላትና በሚመለከታቸው ተቋማት ቅንጅት እንዲፈጽሙ የማድረግ አቅጣጫን እንከተላለን።

# 9. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና መፍትሄዎች፤

## 8.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፤

- የኤም ኤስ ሲ ዘን አለመዘርጋት የተዘረጋባቸውም ቢሆን የኢንተርኔት መቆራረጥ / የሲስተም አለመዘርጋትና መቆራረጥ፣
- ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል እየተሰጡ አለመሆኑ፣
- የግብዓት ችግር፣
- የሰው ሀይል ዕጥረት፣
- የክህሎት ማነስ፣
- የቢሮ አገልግሎት አሰጣጥ አመቺ አለመሆን፣

## 8.2 ችግሮችን ለመፍታት የምንጠቀመው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

- በሁሉም ወረዳዎች የኤም ኤስ ሲ ዞን ዝርጋት እንዲያገኙ ማድረግና የሲስተም መቆራረጥ እንዳያጋጥም ከሚመለከተው የአይሲቲ ክፍል ጋር በቅርበት መስራት፣
- በሁሉም ወረዳዎች በተጠናው ቢፒአር ጥናት መሰረት መደቡ የሚጠይቀው የሰው ሀይል እንዲሟላ በማድረግ በአንድ ማዕከል ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ማዕከሉ በተሟላ አቅሙ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ግብዓት እንዲሟላላቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ወደ ማዕከሉ የተቀላቀሉ የአንደ ማዕከል ባለሙያዎች የአቅም ግንባት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ማዕከሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው የቢሮ አወቃቀር እንዲኖረው በቅርበት መከታተል፣

# 10. የክትትልና የድጋፍ አግባቦች

## 10.1. በመስክ ወርዶ መደገፍ

- በከተማ የሚገኙ ዳይሬክተር ፤ ቡድን መሪዎች ክፍለ ከተሞችን ስራው ያለበት ቦታ ድረስ በመሄድ ይደግፋሉ የቃል ፊድባክ ይሰጣሉ፣
- በከተማ ደረጃ ያሉ ዳይሬክተርና ቡድን መሪዎች በተዋረድ ክፍለ ከተማንና ወረዳን ማብቃት እንዲሁም ተግባራቶች ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ዋነኛ ተልዕኳቸው መሆኑን ተገንዝበው ወርደው እንዲሰሩ ይደረጋል፣ ይህም በመደበኛ ስራነት እንጂ ወቅታዊ ተልዕኮ ወስደው እንደፈፀሙት መታየት የለበትም፤ በዚህም ዕለታዊ፣ ሳምንታዊና ወርሃዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ አሠራርም መዘርጋት፣
- በተመሳሳይ ክፍለ ከተሞች ወረዳን የማጠናከሩን ስራ በዚሁ አግባብ እንዲሄዱበት ማድረግ፣
- የሌሎች ተቋማት ድጋፍም በተቀናጀ መልኩ እንዲከናወን አስፈላጊውን ክትትል ይደረጋል ፤

## 10.2 ግምገማ

- የከተማው የስራ ዕድል ፈጠራና አንድ ማዕከል ዘርፍ የስራ ዕድል ፈጠራ ዳይክቶሬት በክፍለ ከተማ ቡድን መሪዎች ጋር በየሳምንቱ ሃሙስ ጠዋት እየተገናኘ ከየዘርፉ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መሰረት ስራን ይገመግማል አቅጣጫን ያስቀምጣል፣ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን ይወስናል፡፡
- የከተማው ዳይክቶሬት ቡድኖች እና ፈፃሚዎች በየወሩ ተግባሩ የደረሰበትንና አፈጻጸሙን እየገመገመ ይሄዳሉ፡፡
- የለውጥ ቡድኖች በሳምንት አንድ ጊዜ የሞርኒንግ ብሪፊንግ አደረጃጀቶችን በየእለቱ ስራቸውን እንዲሁም የአደረጃጀታቸውንና የግለሰብ ፈጻሚን ውጤታማነት ከስታንዳርዱ አኳያ ይገመግማሉ፡፡
- የሰራተኛ መድረክ በየወሩና በየሩብ አመቱ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡
- የከተማው ዳይሬክቶሬት በየሩብ ዓመቱ ከክፍለ ከተማ እና እንደአስፈላጊነቱ ከወረዳ ቡድን መሪዎች ጋር ስራ አፈፃፀሞችን ይገመግማሉ ፡፡

## 10.3 የሱፐርቪዥን ስርዓት መተግበር፤

- አጠቃላይ ሱፐርቪዥን ስራ አስቀድሞ በተዘጋጀ ቼክሊስት መሰረት በየሩብ ዓመቱ በዓመት አራት ጊዜ ይካሄዳል ፡፡ ይሄውም የስራ እድል ፈጠራ እና ሌሎች ተያያዥ አፈፃፀሞች ተዓማኒነትን እና የሪፎርም ስራው ላይ በማተኮር ይሰራል ፡፡
- ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋትና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንጻር እንደሁኔታው አጫጭር ሱፐርቪዥን ሥራዎች እንዲካሄዱ ይደረጋል፤
- የሱፐርቪዥኑ ሪፖርት ሁሉም ሱፐርቪዥን የተሰራባቸው ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች በተገኙበት እንዲቀርብ ተደርጎ ትምህርት ይወሰድበታል፡፡ በመቀጠልም የማስተካከያ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር እንዲገባ ይደረጋል ፡፡

## 10.4 የጽሑፍ ሪፖርትና ግብረ-መልስ፤

- ሳምንታዊ የስልክና የቃል ሪፖርት ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፣
- በየሳምንቱ ከየክፍለ ከተማ ቡድን መሪዎች ጋር የሚካሄድ ግምገማዎች አጭር የጽሁፍ ሪፖርት እንዲቀርብ ይደረጋል፣

- በየወሩ በሚካሄዱ ግምገማዎች የተጠናቀረ ወርሃዊ ሪፖርት እንዲቀርብ ይደረጋል፣
- የየሩብ አመቱና ዓመታዊ ሪፖርትም በተመሳሳይ ሪፖርት ይቀርባል፣
- ከወርሃዊ ሪፖርትና ግምገማ ተነስቶም የጽሁፍ ግብረመልስ የሚሰጥ ይሆናል፤ በተጨማሪም ወርዶ የሚደግፍ አካል የጽሑፍ ግብረመልስ ይሰጣል፣
- በቃል የሚሰጡ ግብረመልስ በየዕለቱ ከሚታዩ እንቅስቃሴዎች በመነሳት ሊሆን ይችላል።

## 11. ማጠቃለያ

እስከ 2017 የአምስት ዓመት ስትራተጂክ ዕቅድ እንደተመላከተው አሁን ያለውን የስራ አጥ ምጣኔ 18 በመቶ ወደ 14 በመቶ ለማድረስ እንዲቻል የ2013 በጀት ዓመት ዝርዝር ተዘጋጅቷል። ዕቅዱን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ እና የህረተሰቡን እርካታ ለማምጣት በየደረጃው ያሉ አመራርና ፈፃሚዎችንበስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ አጠቃላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ፤ በስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ላይ ሚና ያላቸውን ማለትም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፤

በየደረጃው ያሉ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤቶች፤ በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚሰሩ ተቋማት፤ የግል ተቋማት እና የመሳሰሉትን በማቀናጀት ኢንተርፕራይዞች የስራ ዕድልየመፍጠር አቅማቸውን ሊያሳድግ በሚያስችል ሁኔታ ስራዎችን መስራት ይጠበቃል። በተጨማሪም የስራ ፈላጊውን አመለካከት ለመለወጥ የሚያስችል ስራዎችን በመስራት ስራ ፈላጊውን ለስራ ዝግጁነት ማሳደግ ያስፈልጋል ። ለዕቅዱ ተፈፃሚነትም እቅዱን ማስተግበሪያ ድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት እና ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ አግባብ ስርዓትን በመጠቀም ወደ ተግባር መግባት ይጠበቃል። በአጠቃላይ ለስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ ስኬት የአመራሮችና ፈጻሚዎች በተለየ ቁርጠኝነትና ዝግጁነት መረባረብ በከፍተኛ ሁኔታ መተግበር የግድ ይላል ።